# የደንቆሮ አበጋዝ

ያዳቆነ ሰይጣን ፣ ሳያቀስ እንዲሉ
ዳቦ ሲልስ ያድራል ፣ ሌባ ሰው ላመሉ
ልክን አለማወቅ ፣ እንዲህ ነው ሲቀሉ
ሰው ይጠራ ቢባል ፣ እራሱ መጣ አሉ
ያቀንቃኝ እርካሽ ፣ ዘረኛው ሃጫሉ ።

አተላ የሞላውን ፣ ጭንቅላቱን ይዞ
በባዶ ጥላቻ ፣ ቂም በቀል አርግዞ
በመሃይምነት ፣ የፊጥኝ ተይዞ
መርዛማ ምላሱን ፣ አለልክ መዞ
አቲዮ ባቲዮ ፣ ተረቱን ተናዞ
እንዳበደች ውሻ ፣ መድረክ ተወዝውዞ
ቅርሻት ባደባባይ ፣ በጥላቻ ጦዞ ።

አይቼ ቢቀፈኝ ፣ ሰይ ባንከረባብት
ከመስመር የወጣ ፣ ያሻዋል ስንብት
ቤቴ ነው ያመጣል ፣ ደባል ሲሰነብት ።
ትንሹ ሰው አብጦ ፣ እንዲያ ተከምሮ
ልቡም ጭንቅላቱም ፣ ከጨለማ ጠቁሮ
ዙሪያውን እንዳያይ ፣ አይኖቹ ታውሮ
ሰላምና ፍቅር ፣ የማያውቅ ደንቆሮ
መንጫጫት አበዛ ፣ ቅል እራስ ቆርቆሮ
ሃጫሉን አሰማን ፣ አልሰማ አይል ጆሮ
መርዙን ማስተፋት ነው ፣ እጅና እግሩን አስሮ
ውጤት አይገኝም ፣ ደነዝ አስተምሮ
ገንብቶ ማፍረስ ነው ፣ ማባዛት በዜሮ ።

ግርማ ሞገስ የለው ፣ ወይ ገዝፎ አያስፈራ
ልክና ድንበሩን ፣ የማያውቅ ኩታራ
ተወጣጠረብን ፣ ተሞልቶ በጉራ ።
በፍቅር መድረክ ላይ ፣ ጥላቻን ያወራል
አንድነት ሲተከል ፣ ልዩነት ይዘራል
እሩጫው ሲያበቃ ፣ መሮጥ ይጀምራል
ሰው ነገን ያልማል ፣ ትላንትን ያወራል
በረጅም ሲተለም ፣ እሱ ያሳጥራል
በትንሽ ጭንቅላት ፣ አብጦ ይወጠራል
ስፍራውን የማያውቅ ፣ በከንቱ ያቅራራል ።

በጎጠኞች ማማ ፣ የተንጠለጠለው
ባርቲ ቡርቲ ተረት ፣ አነግ የደለለው
ኢትዮጵያዊነት ላይ ፣ እውቀት የጎደለው
የራሱን ማንነት ፣ ወዶ ያቀለለው
ደካማ ባህሪው ፣ እየተከተለው
የጎበጠ እምነቱ ፣ በቂም የገደለው
የደንቆሮ አበጋዝ ፣ እውቀት ያልታደለው
ከተሰቀለበት ፣ ዘርጥጦ መጣል ነው ።

ታዛቢው

July 20, 2018